


# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከኖቬምበር 1-10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

# እንዲሁም ከኖቬምበር 11-20፣21-30 የሚኖረዉ የአየር ሁኔታ

# ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኖቬምበር 2025

አዲስ አበባ


ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ


## 1. እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት ለበጋ ዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ የተሻላ ገጽታ ነበራቸዉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሁኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ እንዲሁም በክረምት ወቅት ዝናብ ሲያገኙ የነበሩት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻላ ገጽታ ነበራቸዉ፡፡ በመሆኑም፤ በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ የሚያገኙት የደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎችም በፀሀይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠረው ዝናብ ሰጪ ደመናዎች ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ10 ሚ.ሜ በላይ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አርባምንጭ 20.8፣ 25.2፣ ጎሬ 19.2፣ 18.8፣ 18.1፣ ነቀምት 10.2፣ ሮቤ 14.5፣ አማን 11.9፣ አርጆ 10.2፣ 18.8፣ አሶሳ 54.2፣ አይከል 10.9፣ ቦሬ 16.2፣ ቡለን 20፣ ቡረጂ 15፣ ጨፋ 31፣ ዲላ 25.8፣ ዶሎመና 30፣ ፉኙዶ 32፣ ጋቲራ 14.6፣ ቡሌ ሆራ 29.3፣ ኮንሶ 14.1፣ ላሬ 23፣ ላይብር 11.6፣ 12.2፣12፣ ሊሙገነት 16.6፣ ማጂ 50.8፣ ማሻ 30.4፣ ነጆ 27.3፣ ሳዉላ 32.8፣ ተረጫ 11፣ አባጃራ 20.5፣ 18፣ 12.4፣ አቦሞሪንጋ 11.4፣ 13.4፣ ኣሺ 22.9፣ 12.1፣ ቢላምቢሎ 13.8፣ 17.8፣ ቡልቂ 10.4፣ መንደር ሰባት 13.5፣ 25.7፣ ዲንሾ 13፣ እርምጭ 31.3፣ ፎጉሌቃ 10.2፣ ጌጫ 18፣ 19፣ ጉበቲ 37.3፣ 49.4፣ 12.1፣ ቅዳሜ ገበያ 48.6፣ 32.8፣ 12.5፣ 48.6፣ ኮበን 35.5፣ 33፣ ኩሚ 12.8፣ ሙጊ 14.6፣ 10.1፣ 37.7፣ ኦንጋ 10.2፣ 16፣ ሼንዲ 11.5፣ ትንሹ መጢ 10.2፣ 24.5፣ 11.8፣ መንደር አስራ ሶስት 12.4፣ እንዲሁም መንደር አስራ አንድ 18.5፣ 18.5 ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በአስራ ሁለት (12) የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛዉና ምዕራብ ጎንደር፣ በህር ዳር ዙሪያ፣ በሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ መተከል በጥቂት ቦታዎቻቸዉ ላይ አልፎ አልፎ በነበሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ ከ3-5 ሚ.ሜ የሚደርስ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ከ1-3 ቀናት ያህል ተመዝግቧል (ካርታ 1 )፡፡





ምስል፡1 ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2025 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው


ባለፉት አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት አከባቢዎች የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል የቦረና፣ የምስራቅ ቦረና፣ የጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ከሱማሌ ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ እና ዶሎ ዞኖች ላይ ከ11-60 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-9 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ1 እና 2)፡፡ በተመሳሳይ ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ እያገኙ የነበሩት ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ፣ የወላይታ እና ጌዲዮ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከ31-111 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ ከሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ከኦሮሚያ ክልል የቦረና፣ የምስራቅ ቦረና፣ የጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ላይ በአብዛኛዉ ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር


በሌላ በኩል ባለፉት አስር ቀናት የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አልፎ አልፎ በነበሩት ቀናት በመካከለኛው፣ በሰሜን ምሥራቅ እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች ተመዝግቧል (ምስል 1)፡፡




ምስል፡1 ከኖቬምበር 1-10 በ24 ሰዓት ውስጥ ከሶስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች የተመዘገበባቸዉ ስፍራዎች

## 1.2 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ተስተውሏል። ይህም ሁኔታ የሰብልና የድህረ ሰብል ስብሰባቸውን በሚያካሂዱ በአንዳንድ አካባቢዎች አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር፡፡ በሌላም በኩል በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የነበረው እርጥበት ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍርፍሬ ተከሎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በመኸር ወቅት መጨረሻ ላይ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት በመታገዝ ለሚዘሩ እንደ ጓያ እና ሽንብራ ለመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎች ጠቀሜታ ነበረው። እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ የነበረው እርጥበት በተለይም በደጋማው የቦረናና ጉጂ ዞኖች ለተዘሩ ሰብሎች ምቹ ሁኔታ የፈጠረ ሲሆን፤ በአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻልና የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማከማችት ገንቢ ሚና ነበረው (ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኖቨምበር የመጀመርያዎቹ አሥር ቀናት በተወሰኑ የበጋ እርጠጥበት ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ ከነዚህም በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ መካከለኛ እና ታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛው ገናሌ ዳዋ፣ ታችኛው አባይ፣ እንዲሁም በጥቂት ላይኛው ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች የተሻለ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው። ይህም ሁኔታ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እና የተፋሰሶችን የስነ-ምህዳር ደህንነት ከማረጋገጥ አንጻር አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በመሆኑም በምዕራባዊ እና ደቡባዊ ተፋሰሶች የተሻለ የአፈር እርጥበት መጠን፣ የጅረት ፍሰት እና የውሃ ክምችት ለማሻሻል አዎንታዊ ሚና ነበረው። በአንጻሩ አፋር ደናክል፣ አዋሽ፣ ተከዜ፣ መረብ ጋሽ እና አይሻ ተፋሰሶች በአብዛኛው ደረቅ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ቆይተዋል (ካርታ 5) ።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ያመዝናል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሰሜን፣ ሰሜን ምሥራቅ፣ ምሥራቅ፣ መካከለኛው እና ደቡብ አከባቢዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ይዘወተራል፡፡ በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ፤ ደቡብ ምስራቅ እንዲሁም የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡


## 2.1 እ.ኤ.አ ከኖቬበር 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በሚቀጥሉት የኖቬምበር የሁለተኛዉ አሥር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም በፀሀይ ሀይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ እያገኙ ባሉት የምዕራብ ኦሮሚያ ክልል ዞኖች፣ የጋምቤላ ክልል ዞኖች እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በ24 ሰዓት ውስጥ ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ የሚደርስ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 6)፡፡

በሌላ በኩል ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በተለይም ከሳምንቱ አጋማሽ በኋላ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ አዊ፣ በምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፤ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ ዞኖች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡ ስለሆነም በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች የደረሱ ሰብሎች መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 11-20, 2025
የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 11-20, 2025
የሚኖረዉ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናብ መጠን |
| አሮሚያ | ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ዳዋ፣ ሊበን እና አፍዴር ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| የክረምት ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ ዞኖች | | |

| | | |
|---|---|---|
| አሮሚያ | የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | የአኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| **በጥቂት አከባበቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎች** | | |
| ኦሮሚያ | ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ የሰሜን፣የምዕራብ የሸዋ እና የደቡብ ምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ የአዊ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ትግራይ | በጥቂት የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና የምስራቅ ትግራይ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | በጥቂት ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ ምሥራቅ፣ ሰሜን እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ እንደሚሄድ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ምስል 2)።




ምስል፡2 ከኖቬምበር 11-20 በ24 ሰዓት ውስጥ ከሶስት (3) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች የሚመዘገብባቸው ስፍራዎች

## 2.2 እ.ኤ.አ ከኖቬበር 21 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመጪዎቹ የኖቬምበር የሶስተኛዉ አሥር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በመጨረሻዎቹ ቀናቶች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረና የምስራቅ ቦረና፣ የምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ ምሥራቅ እና የደቡብ ደጋማ

ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ።

## 2.3 እ.አ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በደቡብ ምዕራብ እና ደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረው መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ለወቅቱ የግብርና ስራ እንቅሥቃሴ በአመዛኙ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል። እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት አርብቶ አደሮች እና ከፊል የአርብቶ አደር ዞኖች ላይ የሚጠበቀው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት በአካባቢው ለሚከናወነው የግብርና እንቅስቃሴ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡ ፡ ሆኖም ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

ሠንጠረ ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| **በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ ፣ ጉጂ፣ አፍዴር፣ ዳዋ፣ ሊበን፣ ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ሁሉም ሲዳማ የክልሉ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም<br>• በደጋማ አካባቢዎች ለተዘሩ ሰብሎች እድገት<br>• ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • የአፈር ዉስጥ እርጥበት መጠነኛ መሆን<br>• ከፍተኛ ትነት | • የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል<br>• የእንስሳት መኖ ከሰበል ተረፈ ምርት ማሰባሰብ እና ማከማቸት<br>• ደጋማ አካባቢዎች ሰብሎች በአረም እንይጎዱ የማስወገድ ስራዎችን ማከናወን |
| **የመኸር ሰብል አምራች ዞኖች** | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ካማሺ፣ አኝዋክ፣ መዥንግ፣ ኑዌር፣ ፣ኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ ፣ምዕራብ ኦሞ ፣ የወላይታ፣ ጎፋ እና ጌድዮ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት ለሚዘሩ እንደ ጓያ እና ሽንብራ ለመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎች እድገት<br>• ዘግይተው ተዘርተው ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉ ሰብሎች<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ልምላሜ<br>• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሟላት<br>• የውርጭ ስጋት መቀነስ | • የደረሱ ሰብሎች ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ<br>• ከእርጥበትና ሙቀት ጋር ተያይዞ የዋግ በሽታ ስጋት መኖር | • የደረሱ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች መሰብሰብ<br>• የጥራጥሬ ሰብሎች (ሽንብራ እና ጓያ) እድገትን መከታተል<br>• በደጋና በውይን አደጋ አካባቢ የሰብል በሽታ ክትትል ማድረግ |
| **ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የሚጠበቅባቸው ዞኖች** | | | | |
| ምስራቅ ሐረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣የሰሜን ፣የምዕራብ ሸዋ እና የደቡብ ምዕራብ የሸዋ፣ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ የአዊ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ እና የምስራቅ ትግራይ ዞኖች፣ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ በጥቂት ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ እና ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ | ቀላል መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት<br>• ዘግይተው ተዘርተው ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራት | • በመኸር ሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ላይ አነስተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ<br>• በጥቂት ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ መጨመረ | • የደረሱ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ሰሞናት የመሰብሰብና በአግባቡ የመከመር ተግባራትን ማከናወን<br>• አልፎ አልፎ የውርጭ ክስተት በሚጠበቅባቸው አንዳንድ አካባቢዎች በሰብሎችና በመስኖ በሚበቅሉ አዝዕርቶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ |

## 2.4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀትሉት የኖቨምበር ሁለተኛ አሥር ቀናት የበጋ እርጠጥበት ተጠቃሚ ተፋሰሶች መጠነኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን የተቀሩት ዝቅተኛ እርጥበት ይኖራቸዋል። በመሆኑም ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ተፋሰሰ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች መተግበር ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| የውኃ ተፋሰሶች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| በአብዛኛው፣ ባሮ አኮቦ፣ መካከለኛው እና ታችኛው ኦሞጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አባይ እንዲሁም ገናሌ ዳዋ | መካከለኛ የእርጥበት መጠን | • ለመስኖና ለሃይል ማመንጫ እንዲሁም ለመጠጥ ውሃ መጠነኛ የውሀ አቅርቦት መኖር | • አንጻራዊ የትነት መጨመር | • የሚገኘውን ውሃ ከብክነት እና ከብክለት መጠበቅ<br>• ውሃን በተገቢ ሁኔታ ማሰባሰብ<br>• ከብክነት እንዲሁም ከብለት መጠበቅ |
| በአብዛኛው አዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ አፋር ደናክል፣ ተከዜ፣ መረብጋሽ፣ ኦጋዴን እና አይሻ፣ | ከመጠነኛ እስከ ደረቅ ሁኔታ | | • እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች የውሃ አጥረት<br>• ከፍተኛ ትነት | • የዝናብ ውሃ ከጣራ እና ከመሬት ወለል ማሰባሰብ<br>• የውኃ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም<br>• የሚገኘውን መጠነኛ የዝናበ ውኃ ከብክነት እና ከብክለት መከላከል |